የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

# የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አፈጻጸም መመሪያ

ቁጥር 919/2014

ሰኔ 2014 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና አፈጻጸም መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 919/2014

### መቅድም

የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን ገበያው የሚፈልገውን አቅምና ብቃት ያሟሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአገራዊና ዓለማቀፋዊነት ገበያ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ምሩቃንን በሁሉም የትምህርት መስኮች ለማፍራት እንዲቻል፤

ከአካባቢያዊ፤ አገራዊና ዓለማቀፋዊ ኢኮኖሚ፤ ቴክኖሎጂ ዕድገትና ከማኀበረሰቡ ፍላጎት ጋር እያደገ የሚሄድ ገበያ መር የትምህርት ስርዓት በዘላቂነት ለመዘርጋት፤

የትምህርቱን ጥራት በማስጠበቅ ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ማፍራት በማስፈለጉ፤

ምሩቃን በእውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት የበቁ መሆን አለመሆናቸውን ከተቀመጠው የምሩቃን ፕሮፋይል ጋር በመመዘን ማረጋገጥ ስለሚገባ፤

በፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ሌሎች የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላትን በአግባቡ ማሳተፍ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመሆኑም ትምህርት ሚኒስቴር በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 1152/2011 አንቀጽ 95 ንዑስ አንቀጽ 2 እና አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይህንን የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ፣

## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የከፍተኛ ትምህርት ምሩቃን የመውጫ ፈተና የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 919/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. የቃላት ፍቺ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

2.1 **ብቃት፡** ማለት የአንድን ግለሰብ ወይም ተቋም በተሰማራበት መስክ ወይም ሙያ ዝቅተኛውን የመፈፀምና የማስፈጸም አቅም ወይም ችሎታ እና ተወዳዳሪነትን ያጠቃልላል፡፡

2.2 **ፈተና፡** ማለት በመስፈርት ላይ የተመሰረተ የአንድን ግለሰብ ወይም ተቋም የመፈጸም ወይም የማስፈጸም አቅም ወይም ችሎታን መገምገም ማለት ነው፡፡

2.3 **የመውጫ ፈተና፡-** ማለት በማንኛውም የትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂ ተማሪዎችን ብቃት ለመመዘን የሚሰጥ የማጠቃለያ ፈተና ማለት ሲሆን የማለፊያ ነጥብ ያላገኙ ተማሪዎችን እንደገና መፈተንንም ያካትታል።

2.4 **የድጋሚ ፈተና፡-** ማለት በቅድሚያ የተሰጠውን የመውጫ ፈተና ወስደው የማለፊያ ነጥብ ላላገኙ ተፈታኞች በድጋሚ የሚሰጥ ፈተና ማለት ነው፡፡

2.5 **ምሩቃን፡** ማለት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም የተማሩና የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ማለት ነው፡፡

2.6 **የከፍተኛ ትምህርት ተቋም፡-** ማለት እንደ አግባብነቱ በፌዴራል ወይም በክልልና ከተማ አስተዳደር የሚተዳደር የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እና ሕጋዊ ፈቃድ (እውቅና) ተሰጥቶት የተቋቋመ የመንግስት ወይም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማለት ነው፣

2.7 **የትምህርት መስክ ምድብ፡-** ማለት የተፈጥሮ ሳይንስ ወይም ማህበራዊ ሳይንስ ምድብ ማለት ነው፡፡

2.8 **ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር** ማለት የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡

2.9 **አገልግሎት** ማለት የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ማለት ነው፡፡

2.10 **የጾታ አገላለጽ፡-** በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለጹት ሁኔታዎች በሙሉ ለሴት ጾታም ያገለግላሉ፡፡

## 3. የመመሪያው አስፈላጊነት

አገራዊ የመጀመሪያ ዲግሪ የእጩ ምሩቃን ብቃት ፈተናን በአግባቡ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስችል ስርዓት ለመዘርጋት እንዲቻል ይህንን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል፡፡ በተጨማሪም የመውጫ ፈተናውን በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ ለመስጠት እንዲሁም በፈተና አሰጣጡ ላይ የተቋማትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 4. የፈተናው ዓላማ

ምሩቃን በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ያገኙትን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት አጣምረው ብቃታቸውን በመፈተሽ በስራው ዓለም ብቁ ተወዳዳሪ፣ በራሱ የሚተማመን፣ ስራ ፈጣሪ እና ዕውቀት አፍላቂ መሆናቸውን ለመመዘን ነው፡፡

### 4.1 ዝርዝር ዓላማዎች

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ይኖሩታል፤

ሀ. በሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት ፕሮግራሞች ላይ በሥርዓት ትምህርት የተቀመጠውን የተመራቂ ፕሮፋይል (የመማር ውጤት) መሟላቱን ማረጋገጥ፤

ለ. ለትምህርት ጥራት ትኩረት በመስጠት እና የትምህርት ውጤቶችን በማሻሻል ለአገራዊ እና ዓለማቀፋዊ ገበያ ብቃት ያለው የሰው ኃይል ማፍራት፤

ሐ. ተመራቂዎች ወደ ሥራ ዓለም ለመቀላቀል የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ ብቃት ማሟላታቸውን መገምገም፤

መ. በሁሉም ፕሮግራሞች ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ምሩቃን ዝቅተኛውን የብቃት ደረጃ ያሟሉ መሆናቸውን በመመዘን ወደ ገበያው/ ኢንዱስትሪው ማቅረብ፤

ሠ. በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ፕሮግራሞች ጥራትና ደረጃ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ጤናማ የውድድር መንፈስ መፍጠር ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ለመውጫ ፈተና ብቁ ስለመሆን እና የፈተናው ሂደት

### 5. ለመውጫ ፈተው ብቁ ስለመሆን

5.1 ህጋዊ እውቅናና ፈቃድ በተሰጣቸው የግልና የመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እውቅና ባላቸው የትምህርት ፕሮግራሞች የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርታቸውን የተከታተሉ፤

5.2 ይህ መመሪያ ጸድቆ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በየትኛውም የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራም (Delivery Modalities) ትምህርታቸውን በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ ተከታትለው ያጠናቀቁ፤

5.3 በከፍተኛ ትምህርት ቆይታቸው ሁሉንም ኮርሶች ወስደው ያጠናቀቁ ወይም የመጨረሻ ዓመት የሁለተኛ ሴሚስተር ላይ ተመዝግበው በመማር ላይ ያሉ፤

5.4 በመጀመሪያ ወይም በባለፈው ዙር ፈተና የማለፊያ ነጥብ ያላስመዘገቡና ድጋሚ እንዲፈተኑ የተፈቀደላቸው፤

### 6. ምዝገባና የፈተና አሰጣጥ ስርዓት

6.1 ከላይ በአንቀጽ 5 የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተፈታኞች ለፈተናው በተቋማቸው በኩል ወይም ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው የበይነ መረብ ቴክኖሎጂ በኩል በተያዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይመዘገባሉ፤

6.2 ተፈታኞች ከተመዘገቡ በኋላ በሚወጣው የመውጫ ፈተና ፕሮግራም መሰረት ለፈተናው በተዘጋጁት የፈተና ማዕከላት በአካል በመገኘት ወይም በበይነ መረብ ይፈተናሉ፤

6.3 ፈተናውን ለመጀመሪያ ጊዜ የሚወስዱ የመደበኛ ተማሪዎች ትምህርት ሚኒስቴር በሚያዘጋጃቸው የፈተና ጣቢያዎች ይፈተናሉ፤

6.4 የድጋሚ ተፈታኞች ፈተናውን ለመውሰድ ከመረጡት የፈተና ጣቢያ ውጭ በሌላ የፈተና ጣቢያ መፈተን አይቻልም፤

6.5 ማንኛውም ተፈታኝ ለፈተና ሲቀርብ ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ካርድና ለፈተና የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጫ ይዞ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

### 7. የመውጫ ፈተና አስተዳደር

7.1 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አካዳሚያዊና አስተዳደራዊ ነጻነትን ሙሉ በሙሉ እስከሚያገኙ እና ፈተናውን በራሳቸው አቅም ማስተዳደር እስከሚችሉ ድረስ የመውጫ ፈተናው በትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት ይሰጣል፤

7.2 የሙያ ማህበራት ተጠናክረው ሙያዊ አበርክቶ መስጠት የሚችሉበት ደረጃ ሲደርሱ በመውጫ ፈተናው ውጤታማነት ላይ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ስልት ይዘጋጃል፤

7.3 በተለያየ ምክንያት የመውጫ ፈተና ያልተፈተኑትን ጨምሮ ፈተናው በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰጣል፤ ሆኖም ግን እንደ ትምህርት ፕሮግራሞች ልዩነት የመውጫ ፈተናው በዓመት ከዚህም በላይ ሊሰጥ ይችላል፤

7.4 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈተናው በክላስተር ደረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7.5 በሙያ ማህበራት ወይም በሌሎች ሴክተር መስሪያ ቤቶች የሚሰጡ የሙያ ፈቃድ ማረጋገጫ ፈተናዎች ጋር የመውጫ ፈተናውን በቅንጅት ሊሰጥ የሚችልበት ስልት ሊቀየስ ይችላል፡፡

## 8. በመውጫ ፈተናው የሚሸፈኑ የብቃት ወሰኖች

8.1 የምሩቃን የመውጫ ፈተና ሲዘጋጅ እንደየ ትምህርት መስኩ ባህሪ በስነ ትምህርት በሚታወቁት የብቃት ወሰኖችን (Scope of Learning Domains) መሰረት ይዘጋጃል፤

8.2 የመውጫ ፈተናው አዘገጃጀት በዋናነት በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የተገለጹትን ቁልፍ የመማር ውጤቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፤

8.3 ፈተናው Cognitive, Psychomotor ወይም Affective የሚባሉ የብቃት ወሰኖችን እንዲለካ ሆኖ ይዘጋጃል፤

8.4 የፈተናው ይዘት በትምህርት መስክ ባለሙያዎች እና በፔዳጎጂ ባለሙያዎች ይገመገማል፤

## 9. የመውጫ ፈተናው ይዘትና የሚያካትታቸው ኮርሶች

9.1 ፈተናው የምሩቃንን ፕሮፋይል፣ እንደ ትምህርት መሰኩ ባህሪ በስነ ትምህርት በሚታወቁት የብቃት ወሰኖች (Scope of Learning Domains) እና በገበያው የሚፈለገውን ዝቅተኛ መስፈርት (ስታንዳርድን) መሰረት ያደረገ ሆኖ ይዘጋጃል፤

9.2 በመውጫ ፈተናው ውስጥ የሚካተቱት የኮርስ ዓይነቶች በየትምህርት መስኩ በሚዘጋጁ የማስፈጸሚያ ማንዋሎች ላይ እንዲለዩ ይደረጋል፡፡

9.3 በፈተናው የሚካተቱት ኮርሶች ምሩቃን በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት እንዲጨብጧቸው የሚፈለገውን የምሩቃን ፕፋይልን የሚለኩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 10. ፈተናው ስለሚሰጥበት አግባብ

10.1 ፈተናው የጹሑፍና የተግባር ላይ ፈተናን ሊያካትት ይችላል፤ ለፈተናው የሚኖራቸው የነጥብ ድርሻ በየፕሮግራሙ በሚዘጋጀው የፈተና መከታተያ ንድፈ-መለኪያ ላይ (Blue Print) ይገለጻል፤

10.2 ልዩ ብቃትና ዕውቀት ለመመዘን በሚጠይቁ ፕሮግራሞችና የትምህርት መስኮችን የሚለኩ የፈተና ተቋማት ይለያሉ፤

10.3 እንደ ትምህርት መስኩ የተለያየ ሆኖ የተግባር ላይ ፈተና ይዘት በሁሉም ፕሮግራሞች ተግባራዊ እስከሚሆን ድረስ የጹሑፍ ፈተና በስራ ላይ ይውላል፤

10.4 የጹሑፍ ፈተናው የምርጫ (Objective Questions) ጥያቄዎችን እንዲያካትት ሆኖ ይዘጋጃል፤

10.5 ከላይ በአንቀጽ 10.4 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ትምህርት ፕሮግራሙ ዓይነት የፈተናው ይዘተና ቅርጽ ሊለያዩ ይችላሉ፤

10.6 በምርጫ መልክ የሚዘጋጁት ጥያቄዎች የተፈታኞችን እውቀት፤ ክህሎትና አመለካከት በትክክል የሚለኩ መሆናቸውን በዘርፉ ባለሙያዎች ይገመገማሉ፤

10.7 ፈተናው በቴክኖሎጂ፤ በበይነ መረብ፤ በወረቀት ወይም ቅይጥ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊሰጥ ይችላል፤

## 11. የፈተናው ፋይዳ/ተጽዕኖ

11.1 በሁሉም የትምህርት መስኮች የማለፊያ ነጥብ ሳይንሳዊ መንገድን የሚከተል ሆኖ 50% ዝቅተኛው የማለፊያ ነጥብ ይሆናል፤

11.2 እንደ ትምህርት መስኩ ተጨባጭ ሁኔታ ከ50% በላይ የማለፊያ ነጥብ ለሚጠይቁ መስኮች የማለፊያ (የመቁረጫ) ነጥቡ በየጊዜው ሊወሰን ይችላል፤

11.3 የመውጫ ፈተና ውጤት በተማሪዎች ሰርተፊኬት (Temporary Degree) ወይም ትራንስክሪፕት ላይ አልፏል (Pass) ወይም ወድቋል (Fail) በሚል እንዲመላከት ይደረጋል፤

11.4 አንድ ተማሪ ለምረቃ ብቁ የሚሆነው የመውጫ ፈተና ወስዶ የማለፊያ ነጥብ ካሟላ ብቻ ይሆናል፡፡

11.5 ተፈታኞች ፈተናውን ወስደው ማለፍ እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ላልተገደበ ጊዜ መፈተን ይችላሉ፤

11.6 ሆኖም ግን የመውጫ ፈተናውን ሶስት ጊዜ ወስደው የማለፊያ ነጥብ ያላገኙ ተፈታኞች በብሔራዊ የብቃት ማዕቀፍ በሚሰጠው እኩሌታ መሰረት ተገቢው ማስረጃ ይሰጣቸዋል፤

## 12. ድጋሜ ስለመፈተን

12.1 የመጀመሪያውን ፈተና ያላለፉ ተፈታኞች ለተጨማሪ ሁለት ጊዜ ፈተናውን በድጋሚ መውሰድ ይችላሉ፤

12.2 ተፈታኞች ፈተናውን በድጋሚ ለመውሰድ ዝግጁ በሆኑበት ጊዜ ለመፈተን አመልክተው መፈተን ይችላሉ፤

12.3 ሆኖም ግን የመጀመሪያ ፈተናውን በወሰዱ ሶስት ዓመታት ውስጥ የድጋሚ ፈተናዎችን መውሰድ ይኖርባቸዋል፤

## 13. ፈተና ለማዘጋጀት የሚጠበቅ መስፈርት

በሁሉም የትምህርት መስኮች የመውጫ ፈተናውን የሚያዘጋጁ አካላት የሚከተለው ፕሮፋይል እንዲኖራቸው ይጠበቃል፤

13.1 በዩኒቨርሲቲ መምህርነት ቢያንስ አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ አገልግሎት ያለው፤

13.2 በትምህርት መስኩ ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው፤

13.3 በትምህርት መስኩ እና በምዘናና ግምገማ ትምህርት ዘርፍ በቂ እውቀት ያለው፤

13.4 ከትምህርት ክፍሉ የስነ ምግባር ጉድለት የሌለበት፤

## 14. የድጋሜ እርማት

14.1 በፈተናው የመጀመሪያ እርማት ላይ ቅሬታ ያላቸው ተፈታኞች በተቋማት በኩል ወይም በበይነ መረብ ቅሬታቸውን ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ማቅረብ ይችላሉ፤

14.2 ከቅሬታዎች መካከል የድጋሜ እርማት ጥያቄ ከቀረበ ፈተናው በድጋሜ ታርሞ ውጤቱ ለተፈታኞች ይገለጻል፤

14.3 ይሁን እንጅ በበይነ መረብ ለሚሰጡ ፈተናዎች የድጋሚ እርማት ጥያቄዎች አይስተናገዱም፤

## 15. አዎንታዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተፈታኞች

15.1 በፈተናው ወቅት እና ከፈተናው በፊት አዎንታዊ ድጋፍ የሚደረግላቸው ተማሪዎች ቀድመው ይለያሉ፤

15.2 አዎንታዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መረጃቸው በምዝገባ ወቅት ለአገልግሎቱ የሚደርሱበት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፤

15.3 ሁሉም ተቋማት ለተማሪዎቻቸው የሚያስፈልገውን ድጋፍ ያደርጋሉ፤ የአገልግሎቱ ተጠሪዎች ደግሞ ድጋፉ መሟላቱን ያረጋግጣሉ፤

15.4 የሚደረጉ አዎንታዊ ድጋፎች ዝርዝር ሁኔታ በሚዘጋጀው የፈተና ማንዋል (Exam Handbook) ውስጥ በአግባቡ ይገለጻሉ፡፡

# ክፍል ሦስት

# የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

## 16. የትምህርት ሚኒስቴር

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚህ ዙሪያ ከመንግስት የተሰጡትን ተልዕኮዎች ለመወጣት የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

16.1 የምሩቃን የመውጫ ፈተናውን አስተዳደር በኃላፊነት ያስተባብራል፤ ይመራል፤ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል፡፡

16.2 የሚመለከታቸውን አካላት በማማከር የመውጫ ፈተናውን ሂደት በሂደት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ስትራቴጂ ይቀርጻል፤ አገራዊ መመሪያዎችንም ያዘጋጃል፤ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፡፡

16.3 የመውጫ ፈተና ስራውን ለማከናወን የሚረዳ በጀት በተቋማት በኩል እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

16.4 ከፈተና ዝግጅት እስከ ህትመት ድረስ የሚኖረው ሂደት ሚስጥራዊነቱን ጠብቆ እንዲከናወን ስልቶችን ይቀይሳል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

16.5 ፈተናው የሚሰጥባቸውን ተቋማት ዝርዝር ያሳውቃል፤ በፈተናው ወቅት የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞችን እና ተፈታኞችን ይወስናል፤

16.6 ለፈተና አስፈላጊ ቁሳቁሶች በተቋማት መሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡

16.7 ከተቋማትና ከአገልግሎት ሰጪው አካል ጋር በመመካከር የመውጫ ፈተና የሚሰጥባቸውን ቀናት ይወስናል፣ የፈተና መርሐ ግብር በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፡፡

16.8 ከአገልግለቱና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በመሆን ፈተናው በበይነ መረብ እንዲሰጥ የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

16.9 በየፈተና ማዕከላቱ ፈተናው ያለምንም ችግር እንዲከናወን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

16.10 ለተለያዩ አገልግሎት የፈተና ውጤቱን ይተነተናል፣ የትንተና ውጤቱን መሰረት በማድረግ ለተለያዩ ጥናታዊ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋል፣ ለፖሊሲና ስትራቴጂ ስራዎች በግብዓትነት ይጠቀማል፣

16.11 ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ጋር በመሆን የፈተና ማንዋል (Exit Exam Handbook) ያዘጋጃል፣ ለሁሉም የባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

16.12 በየዓመቱ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀት ለባለድርሻ አካላት ያቀርባል፣ ያስገመግማል፣ የቀጣይ አቅጣጫዎችም ይቀመጣል፡፡

## 17. የፈተና አሰጣጥ ቴክኒካል ኮሚቴ

ቴክኒካል ኮሚቴው አስራ አንድ አባላት ሲኖሩት አወቃቀሩም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

1. የከፍተኛ ትምህርት የብቃትና ጥራት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ………… ሰብሳቢ
2. ከኢትዮጵያ ትምህርት ምርምር ኔትወርክ (አንድ ተወካይ)……አባል
3. ከትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት (አንድ ተወካይ) ….. አባል
4. ከትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን (አንድ ተወካይ)................... አባል
5. ከመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካዮች (አራት)............አባል
6. ከግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካዮች (ሁለት)................... አባል
7. ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ህብረት የሚወከል (አንድ)..........ፀሐፊ

ቴክኒካል ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሆኖ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ያከናውናል፡-

17.1 ከመንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወከሉ አባላት የተቋማትን በተልዕኮና በትኩረት መስክ ልየታን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ይሆናል፤

17.2 እንዳስፈላጊነቱ ኮሚቴው ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደገና ሊዋቀር ይችላል፤

17.3 በፈተና ማዕከላት በአካል በመገኘት ከየተቋማቱ የበላይ ኃላፊዎች እና ባለሙያዎች ጋር በመወያየት ለፈተናው ሂደት አስፈላጊ ግብዓቶች የሚሟሉበትን ሁኔታዎች ያመቻቻል፡፡

17.4 ፈተናው ከመሰጠቱ አስቀድሞ ፈተናው በሚሰጥባቸው ተቋማት ለፈተና ስራ የሚመጥን መሰረተ ልማት መሟላቱን ያረጋግጣል፤ ለአብነትም በክላስተር ደረጃ የመስክ ምልከታ ያካሂዳል፤

17.5 በተገቢ ሁኔታ መሰረተ ልማት ያልተሟላላቸውን ተቋማት/ የፈተና ማዕከላት በመለየት እንዲሟሉ ጥረት ያደርጋል፤ ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ሲያጋጠሙ ለሚኒስቴሩ በሪፖርት ያሳውቃል፡፡

17.6 የተፈታኞችን ምዝገባና ፈተና እንዲሁም ውጤትን በበይነ-መረብ ለማካሄድና ለማሳየት የሚያስችል ሶፍት ዌር (Software) ያዘጋጃል፤ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

17.7 ከተፈታኝ ተማሪዎች ጋር በተያያዘ መረጃዎችን ያሰባስባል፤ ይተነትናል፤ በድህረ ገፅ እንዲያውቁት ያደርጋል፤ ለትምህርት ማህበረሰቡ ይፋ የሚሆኑ መረጃዎችን በመለየት ይፋ ያደርጋል፡፡

17.8 የአፈፃጸም ሪፖርትን በጹሁፍ ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል፡፡

## 18. የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት

18.1 ይህንን የመውጫ ፈተና በገለልተኛነት የሚሰራ መንግስታዊ ተቋም እስከሚቋቋም ድረስ አገልግሎቱ ፈተናውን በውክልና የማስተዳደር ኃላፊነት ይኖረዋል፤

18.2 በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ የተፈታኞችን ሙሉ መረጃ እና የፈተና ውጤቶችን ያደራጃል፤ በአግባቡ ይይዛል፤ ለተፈታኞችና ተቋማት በወቅቱ ያሳውቃል፤

18.3 ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበት በመነጋገር የድርጊት መርሐ ግብር ያዘጋጃል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤

18.4 የፈተና ማዕከላት አስተባባሪዎችን፣ ሱፐርቫይዘሮችንና ፈታኞችን ይመርጣል፣ በፈተና ማዕከላት ይመድባል/ያሰማራል፣

18.5 በፈተና አሰጣጥ ሂደቱ ላይ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲገጥም ከትምህርት ሚኒስቴርና ለዚሁ ተብሎ በተቋቋመው ቴክኒካል ኮሚቴ ጋር በመቀናጀት ችግሮችን ይፈታል፣

18.6 ፈተናውን ለማካሄድ የሚያስፈልገውን አጠቃላይ ወጪዎችን የሚያሳይ ፕሮፖዛል ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድለትም በፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት ስራ ላይ ያውላል፣

18.7 የእርማት ውጤትን መሰረት በማድረግ ለመቁረጫ ነጥብ የሚሆን የውሳኔ ሀሳብ ለትምህርት ሚኒስቴር ያቀርባል፣

18.8 በአገልግሎቱ ደረጃ ምላሽ ለሚያስፈልጋቸው ቅሬታዎች ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፣ ሪፖርትም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀርባል፣

18.9 የመውጫ ፈተናው በበይነ መረብ የሚሰጥ ከሆነ የአገልግሎቱን ኃላፊነት የኢትዮጵያ የትምህርትና ምርምር ኔትወርክ ይረከባል፡፡

## 19. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፡-

19.1 በቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ትምህርታቸውን ተምረው ያጠናቀቁ እጩ ምሩቃን ለፈተናው ይመዘግባሉ፣ ዝርዝሩንም ለትምህርት ሚኒስቴር ወይም ለአገልግሎቱ ያሳውቃሉ፣

19.2 የዩኒቨርሲቲውን ድህረ-ገፅ እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን ለተፈታኞች በወቅቱ ተደራሽ ያደርጋሉ፣

19.3 የድጋሚ ተፈታኞቻቸውን ይመዘግባሉ፣ የፋይናንስ ደንብን ተከትሎ የመፈተኛ ክፍያን ሰብስበው ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ገቢ ያደርጋሉ፣

19.4 የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለመውቻ ፈተና የሚደረግ ወጪን ለመሸፈን ከተማሪዎች/ ተፈታኞች በአገሪቷ የፋይናንስ ህግ መሰረት ገንዘብ ሊሰበስቡ ይችላሉ፣

19.5 ምሩቃኖቻቸውን ለመውጫ ፈተናው ያዘጋጃሉ፣ የሞዴል ፈተናም ይሰጣሉ፣

19.6 የመውጫ ፈተናውን ያላለፉ ተማሪዎቻቸውን በድጋሚ ለፈተናው ያዘጋጃሉ፣

19.7 የአፈፃጸም ሪፖርትን በየጊዜው ለሚመለከተው አካል በጽሁፍ ያቀርባሉ፡፡

## 20. የፈተና ማዕከላት

20.1 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና/ ወይም ሌሎች መ/ቤቶች በመውጫ ፈተና የፈተና ማዕከልነት ሊመረጡ ይችላሉ፡

20.2 በፈተና ማዕከልነት የሚመረጡት ተቋማት የመንግስት፤ የግል ወይም ሌሎች ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

20.3 ተቋማት በፈተና ማዕከልነት የሚመረጡት ፈተናውን ለመስጠት የሚያስችል አደረጃጀትና መሰረተ-ልማት ማሟላታቸው በቴክኒካል ኮሚቴ በኩል ተገምግሞ ሲረጋገጥ ይሆናል፡፡

20.4 ተቋማት ተፈላጊውን መስፈርት መሟላታቸው በቴክኒካል ኮሚቴው በኩል ሲረጋገጥ በፈተና ማዕከልነት እንዲያገለግሉ ይደረጋል፡፡

20.5 የተቋማት ተፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው የሚረጋገጠው ተፈታኞች የመፈተኛ ቦታቸውን (ማዕከላቸውን) ከመምረጣቸው በፊት ይሆናል፡፡

20.6 ፈተናውን በተገቢው ሁኔታ ለመስጠት እንዲቻል የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡

20.7 ከፈተና ማዕከሉ ኃላፊ/አስተባባሪ ጋር በቅርበት ይሰራሉ፡፡

20.8 በማዕከሉ ለሚፈተኑ ለሁሉም ተፈታኞች የመፈተኛ ክፍል ያዘጋጃሉ፡፡

20.9 ሁሉም የመፈተኛ ክፍሎች ለፈተናው ምቹ እንዲሆኑ ያደርጋሉ፡፡

20.10 በመፈተኛ ክፍሎች አካባቢ ፈተናውን የሚያውኩ ሁኔታዎችን ያስወግዳሉ ወይም እንዳይኖሩ ያደራጋሉ፡፡

## 21. በፈተና አሰጣጥ ስራ ላይ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ሥልጣን እና ተግባር

### 21.1 የፈተና ማዕከል ኃላፊ/አስተባባሪ

ተጠሪነቱ ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎት ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ. የፈተና ማዕከሉን የፈተና ስራ በበላይነት ይመራል፤ ይከታተላል፤ ያስተባብራል፡፡ ችግሮችም ሲፈጠሩ መፍትሔ ይሰጣል፤ ከአቅም በላይ ሲሆን ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

ለ. ፈተናውን በሚስጥራዊነት ለመስጠት እንዲቻል በአገልግሎቱ የሚሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ይወጣል፡፡

ሐ. የፈተና ጥያቄ ወረቀቶች፣ የመልስ ወረቀቶችና ልዩ ልዩ ቅፆችን በአግባቡና በሚስጠራዊነት ይይዛል፣ ለሚፈጠረውም ችግር ኃላፊነቱን ይወስዳል፡፡

መ. በአገልግሎቱ ወይም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመገኘት ስለ ፈተና አሰጣጥ ገለጻ ይወስዳል፣ ለፈተና የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን /ሰነዶችን/ በኃላፊነት ይረከባል፡፡

ሠ. የመፈተኛ ክፍሎች እና አካባቢው ለፈተና አሰጣጥ አመቺ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ረ. ፈተናው በበይነ መረብ የሚሰጥ ከሆነ ፈተናውን በአግባቡ ለመስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፈጠሩን (ኮምፒዩተር መዘጋጀቱን) ያረጋግጣል፣

ሰ. የፈተናውን አሰጣጥ በተመለከተ ለሱፐርቫይዘር፣ ለፈታኝ፣ ለፀጥታ አሰከባሪዎችና ለተፈታኞች ገለጻ ይሰጣል፡፡

ሸ. በአንድ የፈተና ክፍል ውስጥ በነፍስ ወከፍ ከተዘጋጀው ኮምፒውተሮች በላይ ተፈታኞች እንዳይኖሩ ሁኔታዎችን ከፈተና ማዕከሉ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ያመቻቻል፣

ቀ. የፈተና መርሐ-ግብሩን ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ይፋ ያደርጋል፣ ፈታኝና ሱፐርቫይዘር በመመደብ በስራው ላይ እንዲሰማሩ ያደርጋል፡፡

በ. በፈተና ማዕከሉ ውስጥ ያሉ ተፈታኞችን፣ ፈታኞችን፣ ሱፐርቫይዘሮችን እና የፀጥታ አሰከባሪዎችን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፡፡

ተ. በፈተና አሰጣጥ ወቅት በግልም ሆነ በቡድን የሚፈፀሙ ጥፋቶችን ከፈታኞችና ከሱፐርቫይዘሮች ጋር በመሆን አስፈላጊውን የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፣ በቅጽ ሞልቶም ለአገልግሎቱ ያሳውቃል፡፡

ቸ. በፈተናው ላይ ለተሳተፉና ክፍያቸው በማዕከሉ ኃላፊ በኩል የሚከፈላቸው ተሳታፊዎችን በመለየት የፋይናንስ ህግን ባከበረ ሁኔታ ክፍያውን ይፈጽማል፡፡

ኀ. ከፈተና ማዕከላት የመልስ ወረቀት የያዙ ፖስታዎች የታሸጉበትን ሸራዎች/ፖስታ በመተማመኛ ፊርሞ ለአገልግሎቱ ያስረክባል፡፡

ነ. የፈተና አፈጻጸም ሪፖርት ለትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልገሎት ያቀርባል፡፡

## 21.2 ሱፐርቫይዘር

ተጠሪነቱ ለፈተና ማዕከሉ ኃላፊ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-

ሀ. በአገልግሎቱ በኩል የተሰጡትን የሱፐርቫይዘሮች ኃለላፊነትና ተግባራትን ተግባራዊ

ያደርጋል፡፡

ለ. ፈታኞችን፣ ተፈታኞችን እና የመፈተኛ ክፍሎችን ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ ፈታናው በተያዘለት አግባብ መካሄዱን ያረጋግጣል፡፡

ሐ. የመፈተኛ ክፍሎች ለፈተና አመቺ መሆናቸውንና ለኩረጃ ምቹ ያልሆኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

መ. ፈተና ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የተመደበባቸውን ክፍሎች፣ ፈታኞችንና ተፈታኞችን ስርዓት ማክበራቸውን ይከታተላል፣ በፈተናው መጨረሻም ለማዕከሉ ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ሠ. ፈተናው በሚሰጥበት ወቅት ከፈታኝ መምህሩ ጋር በመሆን የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይፈታል፣ ከአቅም በላይ ሲሆን ለማዕከሉ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡

ረ. ፈታኝ በተጓደለበት ጊዜ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፈታኝነት ተመድቦ ሊሰራ ይችላል፡፡

ሰ. የፈተና ሥርዓትን ጉድለት የፈፀመ ተፈታኝ ሲያጋጥም የፈተና ደንብ መተላለፊያ ቅጾችን ከፈታኝ ጋር በመሙላት ወዲያውኑ ለማዕከሉ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡

ሸ. የማዕከሉ ኃላፊ የሚሰጠውን ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 21.3 ፈታኝ

ተጠሪነቱ ለሱፐርቫይዘሩ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

ሀ. የመፈተኛ ክፍሎች ለፈተና አመቺ መሆናቸውንና ለኩረጃ ምቹ ያልሆኑ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ለ. የተፈታኞቹን የፈተና መግቢያ ካርድ በማየትና በማረጋገጥ ያስገባል፣ ስማቸውን በመመዝገብ ያስፈርማል፡፡

ሐ. ተፈታኞችን በየመፈተኛ ቦታቸው ላይ ያስቀምጣል፣ የፈተና ሂደቱንም ይቆጣጠራል፡፡

መ. ማንኛውንም ዓይነት የፈተና ደንብ የተላለፈ ተፈታኝ ሲያጋጥም ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ ቅፅ ላይ በመሙላትና በመፈረም ለሱፐርቫይዘሩ ያቀርባል፡፡

ሠ. የፈተናውን መጀመሪያና ማጠናቀቂያ ሰዓት ያስከብራል፣ በየመሐሉ ፈተናውን ለማጠናቀቅ የቀረውን ጊዜ ለተፈታኞች ያሳውቃል፡፡

ረ. በመፈተኛ ክፍል ውስጥ መመሪያውን ከማስከበር ውጪ በፈተናው ህግ የተከለከሉ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን አይችልም፡፡

ሰ. በሱፐርቫይዘሩ የሚሰጠውን ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራት ያከናውናል፡፡

21.4 ፖሊስ/ ጸጥታ አስከባሪ

ተጠሪነቱ ለፈተና ማዕከሉ አስተባባሪ ሆኖ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፤

ሀ. በፈተና ማዕከሉ በመገኘት ከመፈተኛ ክፍል ውጪ/በፈተናው ማዕከል ግቢ እና በዙሪያው/ ያለውን ለፈተና አሰጣጡ ሂደት አዋኪ የሆነን ማናቸውንም ዓይነት እንቅስቃሴ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሲሆን ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

ለ. ከፈተናው ማዕከል አስተባባሪ በሚቀርብለት ጥያቄዎች መሰረት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ወደ መፈተኛ ክፍል ድረስ በመግባት የፈተና ሥርዓቱን ያስከብራል፡፡

ሐ. የፈተና ማዕከሉ አስተባባሪ በወሰነው ቦታ ላይ በመሆን ተገቢውን የፈተና ሥነ-ሥርዓት የማስከበር ስራን ያከናውናል፡፡

መ. ለእርዳታ ካልተፈለገ በስተቀር ወደ መፈተኛ ክፍሎች መግባት ወይም መጠጋት አይችልም፡፡

## ክፍል አራት

## ለፈተናው የሚያስፈልገው በጀት እና የክፍያ አፈፃፀም

### 22. ለምዘናው የሚያስፈልገው የበጀት ምንጭ

22.1 ለተመራቂ ተማሪዎች ለሚሰጠው የመውጫ ፈተና በጀት እና የበጀት ምንጭ በሁለት ይከፈላል፤

ሀ. በመንግስት ዩኒቨርሲቲ ትምህታቸውን አጠናቀው ለመጀመሪያ ጊዜ የመውጫ ፈተና ለሚወስዱ ተፈታኞች የፈተና ማስፈጸሚያ በጀት በተቋማት በኩል የሚሸፈን ይሆናል፤ ይህም በተማሪዎች የወጪ መጋራት ላይ እንዲካተት ይደረጋል፡፡

ለ. በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በኩል ፈተናውን የሚወስዱ ተፈታኞች ደግሞ ለፈተናው የሚያስፈልገውን ወጪ በተፈታኞች በኩል ይሸፈናል፡፡

ሐ. የመጀመሪያውን የመውጫ ፈተና ያላለፉና ፈተናውን በድጋሚ የሚወስዱ ተፈታኞች የማስፈጸሚያ በጀት በተፈታኞች በኩል ይሸፈናል፡፡

## 23. የበጀት አስተዳደር ስርዓት

23.1 የበጀት አስተዳደር ስርዓቱ የመንግስትን የፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት አድርጎ የሚፈጸም ሲሆን ፈተናው ለሰብዓዊ እና ቁሳዊ ወጪዎችን የሚሸፍን ይሆናል፡፡

23.2 በመመሪያው ላይ ሰብዓዊና ቁሳዊ ተብሎ ለተጠቀሱት የክፍያ ወጪዎች ተመን በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል እየተጠና ይወሰናል፡፡

23.3 ለፈተና ስራው የሚወጡ ወጪዎች በሙሉ በመንግስት የፋይናንስና ግዢዎች መመሪያ መሰረት ተግባዊ ይደረጋሉ፡፡

23.4 የመውጫ ፈተናውን በዘላቂነት ተግባራዊ ለማድረግ እና ወጪዎችን ለመሸፈን የሚያስችል ህጋዊ የክፍያ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 24. ተጠያቂነት

በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በማንኛውም ሁኔታ የጣሰ፣ እንዲጣስ ያደረገ፣ በማንኛውም ደረጃ ያለ አስፈጻሚና ፈጻሚ አካል በአገሪቱ ባሉ ህጎች፣ ደንቦችና አስተዳደራዊ መመሪያዎች መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 25. የተፈፃሚነት ወሰን

25.1 ይህ የከፍተኛ ትምህርት የመውጫ ፈተና መመሪያ በሚመለከተው የመንግስት አካል ፈቃድ በተሰጣቸው የትምህርት መስኮች የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህታቸውን ተከታትለው ያጠናቀቁ ተማሪዎችን ይመለከታል፡፡ በሁሉም የትምህርት መስጫ ዘዴዎች (Modalities) ትምህርታቸውን የተከታተሉ እጩ ምሩቃን ፈተናውን ይወስዳሉ፡፡

25.2 ይህ መመሪያ በሁሉም የመንግስትና ከሚመለከተው የመንግስት አካል ህጋዊ ፈቃድ የተሰጣቸው የግል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

25.3 ይህ የመውጫ ፈተና ከ 2015 ዓ.ም ጀምሮ ባሉ ሁሉም የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቃን ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 26. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የትምህርት ሚኒስቴር መመሪያውን በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 27. መመሪያውን ስራ ላይ ስለማዋል

ይህ መመሪያ በትምህርት ሚኒስትር ከጸደቀበት ሐምሌ 1/2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርሀኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)
የትምህርት ሚኒስትር